# ኢሕአፓ በቺካጎ የተሳካ ሕዝባዊ ስብሰባ አካሄደ

**ከሚድ ወዌስት የፓርቲው ኮሚቴ**

በትላንትናው እለት (July 19, 2008) ውብ በሆነችው ቺካጎ ከተማ ላይ የሚድ ዌስት የኢሕእፓ ኮሚቴ በጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ በርካታ ኢትዮጵያውያን ተገኝተው የተሳካ ውይይት አካሂደዋል። በዚህ ስብሰባ ላይ ወጣቶችና ሴቶችም ከመገኘ ታቸውም ባሻገር ጥያቄ በማቅረብና ገንቢ ሃሳብም በመሰንዘር ተሳትፈዋል። ያገር ጉዳይ ሆኖባቸው ከቺካጎ ኢትዮጵያዊ ስብሰባ ላይ ተሳታፊ ለመሆን ከሚቺጋን ከሚኖሶታ ከዲሲና ከሴንት ሉዊስም የተገኙ እንግዶችም ነበሩ።

የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባል የሆኑት አቶ ኢያሱ አለማየሁ ሰለ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ማለትም ስለ ወያኔ እምባገነናዊ የግፍ አገዛዝ፡ በቅርቡ ወያኔ ለሱዳን አሳልፎ ስለለገሰው የድንበር መሬታችን፡ ኢሕእፓ ስለ ግንባር (ሕብረት) ያደረገው መስዋዕትነትና በመሰል አንገብጋቢ ችግሮች ላይ በተለመደው የበሰለ አቀራረቡ ለታዳሚው አቅርቧል። ቀጥላም በኢሕአፓ ሰራዊት ውስጥ ለደርግና ለወያኔ ሰራዊት የራስ ምታት የነበረችዋ ጀግናዋና ስመ-ጥሩዋ አለም ከበደ ወይም (የሜዳ ስሟ አያልነሽ) ስለ ውጣቶችና ሰለ ሴቶች ወሳኝ ሚና ተገቢውን ግንዛቤ ለስብሰባው ተሳታፊዎች በሚገባ አቅርባለች።

በተለይም ድንበራችንን በተመለከት ሁለቱም ተናጋሪዎች ቀደም ሲል ኢሕእፓ ካካባቢው ሕዝብ ጋር በማበር ሰራዊቱ የሱዳንን የድንበር መሬት ምኞት በጀግንነት ማክሸፉቸውን ገልጸዋል። ኢሕአፓ የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ አይደለም በማለቱ በሻቢያና በወያኔ የተሰነዘረበትን ጥቃት፡ ደርግ በወያኔና በሻቢያ ጉልበቱ እየመነመነ ሲመጣ ኢሕእፓ ሃገርን ከጥፋትና ከውርደት ለማዳን ሲል ብቻ ከደርግ ጋር ላለመዋጋት የሰላም ጥሪ ቢያቀርብም እንኳን ደርግ እስኪሞት ድረስ ኢሕእፓን ሲወጋ እንደነበርና ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው ደገሞ ባንድ ጊዜ በኢሕእፓ ላይ በሱዳን ሰራዊት በሻቢያ በወያኔና በደርግ ይህነው የማይባል ጦርነት መካሄዱ ነበር። ኢሕአፓ ዛሬም አለሁኝ የሚለው ከዚህ ሁሉ ጥቃት ተርፎ ነው። ኢህአፓ በሳት የተፈተነ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጇ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው በማለት ሁለቱም ተናጋሪዎች የድርጅታቸውን ገድል በሚገባ ለተሰበሰበው ሕዝብ አሰምተዋል።

ከሁለቱ ተናጋሪዎች በተደጋጋሚ ጫና ተሰጥቶ የተደመጠው **የኢትዮጵያ መሰረታው ችግር ወያኔ** በመሆኑ ወያኔን በሕዝባዊ ሃይል ጥለን ዲሞክራሲያዊ ኢትዮፕጵያን መመስረት ለነገ የማንለው ጉዳይ ነው የሚለው ነበር። ወያኔን መግራት ይቻላል ወይም ማለሳለስ ይቻላል የሚሉ የዋህ ተቃዋሚ ነን የሚሉ ሃይሎች ከብዥታቸው መውጣትም እንዳለባቸው አስምረውበት ተናግረዋል።

በስብሰባው ላይ የተገኘው ታዳሚ ይነበብበት የነበረው ያገርፍቅር ስሜትና ከስሜትም ባሻገር ይሰጠው የነበሩት ገንቢ የተግባር ሃሳቦች እጅግ በጣም ገንቢ ነበሩ። በስበሰባው የተገኘው ሕዝብ ለኢሕአፓ ያሳየው የሞራልና የገንዘብ ድጋፍ በጣም የሚያበረታታ ነበር።

የቺካጎ ሕዝብና ካካባቢው የመጡት ኢትዮጵያውያን ለቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታ ለሆነ ኢሕአፓ የሰጡን ድጋፍ የስብሰባው አዘጋጅ ኮሚቴ ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል።

## ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!!!